# ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
# Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)

Website: www.moreshwegenie.org E-mail: hq-office@moreshwegenie.org


ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

April 18, 2020

## ለውድ የክርስትና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን በሙሉ፥

**እንኳን ለ2012 ዓ/ም የጌታችን የመዳህኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የትንሳኤ (ፋሲካ) በአል በሰላም አደረሳችሁ!!!**

በሞረሽ ወገኔ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና በራሴ ስም ይህ አውደዓመት የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የመተሳሰብ፣ የብልጽግና፣ የደስታ፣ በተለይም የጤና እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞታችንን እየገለጽን፤ ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያም ለልጆቿ አንድነትንና ትብብርን ሰጥቶ፣ ከቤታቸው ወጥተው በሰላም የሚገቡበት፣ ከቤት ንብረታቸው ተገፍተው የወጡ ፍትህ የሚያገኙበት፣ ያዘኑ የሚጽናኑበት፣ የተራቡ የሚመገቡበት፣ የታመሙ ፈውስን የሚያገኙበት ጊዜ እግዚአብሔር ያሰፍንልን ዘንድ ልባዊ ምኞታችንን እንገልጻለን።

በተለይ በሲቪክ ድርጅትነት ሞረሽ ከቆመለት ራዕይ አንጻር፥ በኢትዮጵያ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሙሉ በሀገራችሁ የትኛውም ጥግ ተዘዋውራችሁ የመሥራት፣ የመበልጸግ፣ ቤተሰብ የመመስረትና፣ በሰላም የመኖር መብታቸችሁ ይከበር ዘንድ በአንድነት እንድትቆሙ፤ አንዱ ኢትዮጵያዊ የሌላው ኢትዮጵያዊ ጠባቂ መሆኑን በማሰብና ነባር እሴቶቻችሁን ተጠቅማችሁ ሁላችሁም የወገን አልኝታና መከታ በመሆን ይህን ክፉ ጊዜ ቶሎ ታሳልፉት ዘንድ የእግዚአብሔር ፍቃዱ ይሁንልን።

ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ ተከስቶ፣ ዓለምን ያስጨነቀው የወረርሽ በሽታ ድባብ ተገፎ፤ የሚቀጥለውን የፋሲካ በአል በተለመደው ክርስቲያናዊ የአምልኮ ሥነስርአትና ሰፊ ማህበራዊ ህይወት በጋራ ማእድ የምንቋደስበት ሁኔታ እንዲሆን መድሐኒዓለም ምህረቱን ያምጣልን።

በድጋሚ መልካም የ2012 ዓ/ም ፋሲካ በአል ይሁንላችሁ!!!

ከአክብሮት ጋር

አረጋኸን ንጋቱ (ዶ/ር)
የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት ሊቀመንበር